**KINIJIT DC-METRO SUPPORT CHAPTER**
*"Serving Washington DC, Maryland and Virginia"*
766 Rock Creek Church Rd. NW
Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556   Fax:  (202) 541-0557 Email: kinijitdc@kinijitdc.org

# ግንቦት 7 እና የኢትዮጵያ ሕዝብ!

ግንቦት 7 ቀን በታሪካችን ውስጥ አንድ ልዩ ምዕራፍ ይዞ ይኖራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በስተቀር ሌላ ሥርዓትን ዳግም እንደማያስተናግድ፤ ለከፋፋይ ፖለቲካ ቦታ እንደሌለው፤ እኩልነት በሰፈነበት አየር ውስጥ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ያለውን ቁርጠኛ ሃሳብ በግንቦት 1997 ዓ/ም ምርጫ ወቅት በጉልህ አሳውቋል። የጧት ቁርና የሌት ሃሩር ሳይበግረው፤ ብዙ ኪሎሜትር በግሩ ተጉዞና ሥርዓትን አክብሮ ብርቅየ ምርጫ ካርዱን የፍላጎቱ መግለጫ ማድረጉ ሕብረተሰቡ የሚገኝበትን የብስለት ደርጃ መስክሯል።

ይሁን እንጅ የሕዝቡን የብስለት ደረጃና የውስጥ ፍላጎቱን ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እኩል ተረድተውት ነበር ማለት አይቻልም። አንዳንድ ወገኖች ዲሞክራሲን የይስሙላ ግብዣና ካንዱ ለሌላው እየተቀነጠረ የሚለገስ ምንዳ አድርገው አይተውት እንደነበር ከተግባራቸውና ከደረሱት አሳዛኝ ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል። በዚህ ረገድ ስለሃገሪቱ ፖለቲካ፤ ማሕበራዊና ኤኮኖሚያዊ መልክአ-ምድር ከማንም የተሻለ ቅኝት የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለዚህ ነው የቅንጅት ራእይ ከሕዝብ ራእይ ጋር ባንዴ የሠመረውና በቅንጅትና በሕዝብ መሃከል ጠንካራ ውል ሊፈረም የቻለው።

ሌላ ቁምነገርም አለ። የሕዝብን ስሜትና ፍላጎት ጠንቅቆ ለመረዳትና ይህን ፍላጎት እውን ለማድረግ የሚያስችል ራእይ ለመቅረጽ በሳልና ሕዝብን ከማገልገል በስተቀር ሌላ አጀንዳ የሌላቸው ልሂቃን መገኘታችውን ይጠይቅ ነበር። በታሪክ አጋጣሚና በመታደል ጭምር በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰቡት መሪዎች ይህን ያሟሉ ነበሩ። 97 ምርጫ መዳረሻ ላይ የተካሄዱትን ውይቶች መለስ ብለን ብናይ ቅንጅትና ሕዝብ በአንኳር የሃገሪቱ ችግሮችና ተስፋዎች ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ ላይ የደረሱበት ዘመን ነበር ማለት እንችላለን። የቅንጅት መሪዎች በሕዝብና በፓርቲው መሃከል የተደረሰበትን ስምምነትና መግባባት ለመተግበር በተነሱ ነው ለሞትና ልሥራት የተዳረጉት። የተከሰሱበትን የፈጠራ ውንጀል እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም ሕዝብ አውግዞታል። የወያኔ ኢሕአዴግ ደጋፊዎችና አባላት እንኳ ቢሆኑ በልባቸው ልብ ክሱ የፈጠራ መሆኑን የሚዘነጉት አይመስለንም።

ኢትዮጵያ ወደሠላምና ወደብልጽግና ጎዳና ትሸጋገር ዘንድ ብሔራዊ እርቅ መፈጠሩ አማራጭ እንደሌለው በብዙ ወገኖች የተወሳ ነው። ለዚህ ብቸኛ መፍትሔ ተገቢውን አክብሮት የማይሰጡ ወገኖች በሃገሪቱ ውስጥ ሊከሰት በሚችለው ብጥብጥም ሆነ ሁከት ተጠያቂ እንደሚሆኑ ሊዘነጉት አይገባም። የብሔራዊ እርቅ ጎዳና መነሻው አንድና አንድ ብቻ ነው። በግፍ የታሠሩትና የተንገላቱት ሃቀኛ የቅንጅት መሪዎች፤ እንዲሁም ሌሎች የዲሞክራሲ ታጋዮች ያለአንዳች ቅድመሁኔታ መፈታታት አለባቸው። ይህ ለድርድር እንኳ የሚቀርብ አይደለም።

ታሪካዊውን ወርሃ ግንቦት በምናስታውስበት ባሁኑ ወቅት፤ ለመብትና ለዲሞክራሲ በመቆማቸው ብቻ በግፍ የተገደሉ ወገኖቻችንንና ቤተሰቦቻቸውን በአንክሮ እናስባቸዋለን። የከፈሉት መስዋዕትነት በከንቱ እንዳልሆነም ዲሞክራሲና ሠላም የሰፈነባት ኢትዮጵያን በማቋቋም እናረጋግጥላቸዋለን። በእስር የሚገኙት የሕዝብ ተመራጭ መሪዎቻችንም ነጻነታቸውን አግኝተው ለወገናቸው የተለሙትን ራእይ በተግባር ለመተርጎም የሚችሉበት ዕድል እስኪያገኙ ድረስ ትግላችን እንደማያሰልስ ቃልኪዳናችንን እናድስላቸዋለን።

የቅንጅት መንፈስ ለዘልዓለም ይኖራል!
ቅንጅት ዲሲ-ሜትሮ ድጋፍ ቻፕተር
ግንቦት 7 ቀን 1999 ዓ/ም